## ኣንድን የፖለቲካ መስመር መቃወም እና መደገፍ ሊከበር የሚገባው የዴሞክራሲ እሴት ነው።

አንድን የፖለቲካ መስመር በሚከተሉት ፓርቲዎችና ግለሰቦች ላይ  ሂስ ወይም ትችት ማቅረብ ልንለምደው የሚገባ ጠቃሚ ባህል መሆኑን መቀበል አለብን። ዴሞክራቶችን ከአምባገነኖች የምንለይበት ዋናው ሚዛናችንም ይሄው ስለሆነ ሂስ ወይም ትችት የሚቀርብበት የድርጅት መሪም ሆነ የሚመራው የፖለቲካ ተቅዋም ከግለሰብ ዜጎች የሚቀርብበትን ሂስ ወይም ትችት ገንቢውን አመስግኖ መቀበል አፍራሹን አፍራሽ ሂስ ለመሆኑ በቂ ማብራሪያ ሰጥቶ ውድቅ ማድረግ ይገባዋል። ከዚህ ዴሞክራሲያዊ መረህ ውጭ ገምቢም ሆነ አፍራሺ ሂስ ባጠቃላይ ለምን ቀረበብን በማለት ሂስ አቅራቢውን እንደጠላት ማየቱ ግን ተገቢ አይደለም። የአምባገነንነት መገለጫ እንጅ የዴሞክራቶች ሊሆን አይችልምና። ዴሞክራቶች የማንኛውንም ሐሳብ አይገድቡም፥ እንዲያውም ግለስቦች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲናገሩ ያበረታታሉ እንጅ። ግለሰቦች ያላቸው ህሳብ ገምቢና አፍራሽ መሆኑ ሊታወቅ የሚችለውም ከአንደበታቸው ሲወጣ ነው እንጅ ሲታመቅ አይደለም። ይህ ሲባል ግን ትችት ወይም ሂስ አቅራቢው የሚያቀርበው ሂስ ወይም ትችት ገንቢና አፍራሺ መሆኑን በቅድሚያ የመመርመር ሃላፊነት አይጠበቅበትም ማለት አይደለም።

ይችን አጭር አስተያየት በጽሑፍ እንዳቀርብ ህሊናየን ያስገደደኝ ነገር << የአዛኝ ቅቤ አንጓች ወይንስ አህያውን ፈርተው ዳውላውን >>  በሚል አርዕስተ ነገር ፤ በአቶ ‘’ ድሉ ዘገየ ’’ ለከረንት አፌርስ የውይይት መድረክ የቀረበውን ከፊል አፍራሺ ከፊል ገንቢ ሂስ ወይም ትችት በፓልቶክ ስሜ ተጽፎ ሰላየሁ ነው። ይህን ሂስ ያቀረብክ አንተነህ ብለው ብዙዎቹ  ገምተውም ነበር ፥ አሁንም እንዳሉ እገምታለሁ። ነገር ግን ‘ ድሉ ዘገየ’ በሚል ስም የምታዎቀው አይደለሁም ጽሁፉን የፃፍኩት። ጸሓፊው ለምን በሰሜ ለመጻፍ እንደወሰኑ ለመረዳት ተቸግሬአለሁ። በዚህ ስም የሚጠራ ሰው ስለማያቁ ነው እንዳልል ፥ ጸሓፊው እንደኔ የፓልቶክ ታዳሚ ከመሆናቸውም በላይ ፡ ሂስ ላቀረቡበት ክፍልም አድሚን ሁነው እንደሚያገለግሉ ወይም ሲገለግሉ እንደነበር ከጽሑፋቸው ውስጥ ካስቀመጧቸው ጠቋሚ ሀረጎች ለመረዳት ችያለሁ።

ታድያ ለምን ይሆን ያላጡት የብዕር ስም ስሜን ለሂስ ማቅረቢያ ተጠቀሙበት ? ለሚለው ጥያቄ ግን መልስ ማግኘት አልቻልኩም። የወያኔ ካድሬዎች ባለኝ ጠንካራ ፀረ ወያኔ አቋም እንደኔ በፀረ ወያኔ አቋማቸው ከሚታዎቁት ከረንት አፌርሶች ጋር ለማጋጨት የተደረገ ድርጊት ነው እንዳልል ፥ የጸሓፊው ጽሑፍ መሰረታዊ ይዘቱ በወያኔ ካድሬ ብዕር የተቀለመ አይመስልም። ታዲያ ለምን ? ብዬ ለጊዜው ከማለፍ ሌላ ምንም ማድረግ አልችልም። ድርጊቱ ግን በጣም አሳዛኝ እና አስገራሚ ነው። ወደፊትም ለኢትዮጵያውያን አንድነት ከሚታገል ወገን የማይጠበቅና ሊደገም የማይገባው ጥፋት ነው አላለሁ።

በመግቢያየ እንደገለጥኩት በሂስ ወይም ትችት በማቅረብም ሆነ በመቀበል አምናለሁ። ነገር ግን ወገን አውቆ በድፍረት ከሚሰራው ጥፋቱ ፥ ሳያውቅ በስህተት ከሚፈጽመው ስህተቱ እንዲታረም ሌላው ተቆርቋሪ ወገን ገንቢ የሆነ ሂስ ወይም ትችት ማቅረብ መብትም ፥ ግዴታም ነው። ታድያ አቶ ‘ ድሉ ዘገዬ ‘ ይህን መርኀ ተጠቅመው ነው ሂሱን ተቀባዮቹ ወገኖች እንዲቀበሉት ያቀረቡት ? ወይስ አው በአእምሮ ወአው በኢያእምሮ=በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተከፋፈለውን የተቃዋሚ ሃይል በማስተባበር ፋንታ የበለጠ ለመከፋፈል የተደረገ አሳዛኝ ድርጊት? ይህን ጥያቄ ኣዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ትርጉም ባለው መልኩ ለመመለስ በበኩሌ በጣም እቸገራለሁ። ምክንያቱም ግለሰቡ የጠላት መልክተኛ ሁነው ተቃዋሚውን ለመከፋፈል ሆን ብለው ያደረጉት ሙከራ ነው እንዳልል ፥ ሂሱን ያቀረቡት ወያኔን ደርጅታዊ አቅሙና ተጨባጭ ሁኔታው በፈቀደለት መጠን የሚታገለው የአንድነት ፓርቲ ‘’ በከረንት አፌርስ አፍራሺ ሂስ ተሰነዘረበት’’ ብለው ለአንድነት ያላቸውን ወገንተኝነት ለማሳየት የወሰዱት እርምጃ እንደሆነ የጽሑፋቸው ይዘት ያሳያል።

ግለሰቡ ያለተገነዘቡት ነገር ቢኖር ግን ከረንት አፌርሶች የአንድነት ፓርቲ በኀብረ ብሔይራዊ ድርጅትነት ከተመሠረተበት ጀምሮ  ከሁሉም ፓልቶኮች በተለየ ሁኔታ ሁለገብ ድጋፍ ሲያደርጉለት እንደቆዩ ነው። አንድነትን መተቸት የጀመሩት እነአቶ ስዬ አብርሐ ተቀላቅለው የአመራር ኣካሉ አባል መሆናቸው ከተደመጠ በኋላ ነው። ይህን መቃወማቸው ደግሞ የሚጠበቅ ነው። ምክንያቱም አቶ ስዬ አብርሐ አሁን አገራችን ለባዕዳን በርካሺ እየሸጠ ፣

ሕዝባችን የዜግነት መብቱን ገፎ ፣ በጎሳና በጎጥ ከፋፍሎ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን በጎሳ ቀይሮ ፣ እንዳይናገር አፉን ለጉሞ፣ እንዳይጽፍ እጁን አስሮ፣ እንዳይራመድ እግሩን እንደ በቅሎ ቀይዶና የጭቆና ቀንበር ጭኖ እየገዛ ያለውን የባዕዳን ቅጥረኛ ሥርዓት ከገነቡት ግንባር ቀደም የወያኔ መሪዎች አንዱ ስለነበሩ ነው። ይህ እውነታ ሊያስተባብሉት የማይቻል ሀቅ ስለሆነ አቶ ስዬ አሁን የገነባሁትን አስከፊ ሥርዓት ለማፍረስ መጥቻለሁና ተቀበሉኝ ሲሉ ከረንት አፌርሶችም ሆኑ ማንኛውም በዚህ አስከፊ ሥርዓት ብዙ ግፍ የተፈጸመበት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለጊዜውም ቢሆን ቢቃወማቸው የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። አቶ ስዬም ራሳቸው ይህን እንደሚጠብቁና ለዚህም የስእነ አእምሮ ዝግጅት አድርገው እንደመጡ በበኩሌ እገምታለሁ። አመጣጣቸው በእውነት ያን የገነቡትን አስከፊ ሥርዓት ከመሰረቱ ለመንቀል ይሁን ወይም በመጠኑ ለመጠገን አንዳንድ ተጨባጭ እርምጃዎችን እስከሚያሳዩ ድረስ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በትናንትናው ዕይናቸው ዛሬ ቢመለከቱአቸው አቶ ሰዬም ሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወይም ጥርጣሬ የተቀበሏቸው ወገኖች ሊያዝኑ ፣ ከዚያም አልፈው ተበሳጭተው አቶ ስዬ በገነቡት ሥርዓት ብዙ ጸዋትዎ መከራ የደረሰባቸውን ኢትዮጵያውያን ሊዘልፉ አይገባም። አቶ ስዬን በዚህ ሁኔታ  አይደለም በደል ከደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ማቀራረብና ማግባባት የሚቻለው። ረጋ ባለና ትሁት በሆነ አንደበት አሁን አገራችንና ሕዝባችን የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ አይተን እነአቶ ስዬን ይቅርታም ባይጠይቁን ያለፈውን ይቅር ስለ ኢትዮጵያ ብለን እንድንቀበላቸው በሚያደርግ መልኩ የእርቁ ሁኔታ በጥበብ መያዝ አለበት። እነአቶ ስዬና የአንድነት ፓርቲ ይህን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ቁስሉን አክሞ ማዳን እንጅ በሃይል እየነካኩ በማድማት በሺታውን ማስወገድ እንደማይቻል ከሁሉም አስቀድመው መረዳት የሚገባቸው ዐቢይ ነገር ነው።

እኔም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ እነአቶ ስዬን እንደ ተቃዋሚ ለመቀበል ብዙ ነበር የተቸገርኩት። በግልጽም መቃወም ጀምሬ ነበር። ነገር ግን የኢትጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ተገንዝቤ ነው ተቃውሞየን ከቅድመ ሁኔታ ጋር ለጊዜው ያስወገድኩ። ቅድመ ሁኔታየም እነአቶ ስዬ የገነቡትን ጸረ ኢትዮጵያ ሥረዓት ለማፍረስ ቆርጠው መነሳታቸውን ዕለት በዕለት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨባጭ እስካሳዩን ድርስ ነው ። እርሳቸውም ቢሆን ይህን ቅድመ ሁኔታ በዚህ ሥርዓት ብዙ ጉዳት የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ያገራቸው ልጆች እንደሚጠብቁ ይረዳሉ ብየ እገምታለሁ። ፓርቲያቸው አንድነትም ይህን ታሪካዊ ግዴታ እንዲወጡ ትልቅ መሳሪያ ሁኖ እንደሚያገለግላቸውና በዚህ ሂደትም አሁን  እየተቃወሟቸው ካሉት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋርም ጥበብ በተሞላበት ዘዴ እንደሚያስታርቋቸው ባለሙሉ ተስፋ ሁነን ውጤቱን እንጠባበቃለን።  ቢቻል ጊዜውንና አጋጣሚውን ተጠቅመው በሥርዓተ ወያኔ የአካልም ሆነ የስእነ አእምሮ ጉዳት ለደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው እንደ ክቡር ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ይቅርታ ቢጠይቁ የበለጠ ተቃውሞውን ይቀንሰዋል ብየ አምናለሁ። ይህን እንዲያደርጉ ፓርቲያቸው አንድነትም ቢያበረታታቸው መልካም ነው እላለሁ። አቶ ስዬም ቢያንስ ለፓርቲያቸው እድገትና ደኅንነት ሲሉ ቢያደርጉት ክብር እንጅ ውርዴት ሁኖ እንደማይቆጠርባቸው መረዳት የሚያቅታቸው አይመስለኝም። ካልሆነም ከቃል ገቢር ይበልጣልና በገቢር ውጤቱን በተጨባጭ እንድናየው በሚያደርግ መልኩ የነመለሰን የባዕዳን ቅጥረኛ አገዛዝ ለመገርሰስ በሚደረገው ያገር አድንና የቅርስ ጥበቃ ተጋድሎ ድርሻቸውን ተወጥተው ያሳዩን ።

 የከረንት አፌርስ የውይይት መድረክ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንም ሁሉንም ነገር በትግስትና በጥበብ ማስተናገድ አለባቸው ። የሚያምኑበትን የፖለቲካ መስመር የሚከተሉትን ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ሁለገብ ድጋፍ ሲደርጉ እንደቆዩ ለህሊናውና ለእውነት ተገዥ ለሆነ ሰው ሁሉ ሊስተባበል የማይችል ሐቅ ነው። ሆኖም ግን " ከሰው ስህተት ፣ ከብረት ዝገት አይጠፋም " እንዲሉ ፣ ከስህተትም ጨርሰው ነፃ ናቸው ማለት አይደለም። በዚህ መሠረት ከመካከላቸው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አልፎ አልፎ አፍራሺ ሚና የሚጫወቱ አድሚኖች እንዳሉ እኔም በግሌ የተገነዘብኳቸው  ሁኔታወች አሉ። በተቃዋሚው መካከል በየጊዜው የሚፈጠረው ቅራኔ እንዲባባስ የሚያደርጉ፣ አንዱን ተቃዋሚ ድርጅት እውነተኛ ፣ ሌላውን አስመሳይ አብሶም ወያኔ በማለት የሚሰጧቸው አፈራሺ ትችቶች እንዳሉ የአደባባይ ምሥጢር ነው። ይህ ችግር ደግሞ በከረንት አፌርስ ክፍል ብቻ የሚታይ ችግር ብቻ እንዳልሆነ የማያውቅ የፓልቶክ ታዳሚ ያለ አይመስለኝም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፓልቶክ ሩሞች ለስድብ ብቻ እንደሚከፈቱ ግልጽ ነው። ባጠቃላይ ሲታይ ግን ከረንት አፌርስ ብዙ ሃገራዊ ቁምነገሮች የሚሰራበት ኢትዮጵያዊ መድረክ መሆኑን የሚጠራጠር አገር ወዳድ የሆነ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ስለዚህ አቶ ድሉ ዘገየ (ሞክሼ) እንዳሉት

ሥራ ፈት ቦዘኔዎች የሚሰባሰቡበት ቤት አይደለም ። እና በሂሳቸው ውስጥ እነዚህን አፍራሺ ቃላቶች መጠቀማቸው አግባብ አይደለም እላለሁ። ሊያርማቸውና ሊያስተካክላቸው በሚችል ስልት አይደለም ሂሱን ያቀረቡትና ፣ ማንነትወን ግልጽ አድርገው ይቅርታ ሊጠይቋቸው ይገባል የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ። ከረንቶችም ለቀረበባችሁ ሂስ እየሰጣችሁት ያለውን የመልስ ምት አገራችን ኢትዮጵያ ካለችበት ችግር አንፃር አይታችሁ ቀነስ ብታደርጉት መልካም ነው እላለሁ። በመካከላችሁም (በሩማችሁ) ጠንክሮ የቆየውን ፍቅርና አንድነታችሁንም ፈተና ላይ እንዳይጥለው ብታስቡበት መልካም ነው። እነአቶ ስዬ ለእኛ የመከፋፈያ ምክንያት ሊሆኑ አይገባም። አንድ ሁነን ሂደታቸውን መከታተል እንጅ። ትኩረታችን በወቅቱ ጠላታችን ላይ መሆን ይገባዋል። ትላንት ዛሬ አይደለምና ለነገው ስንል የትላንቱን ለጊዜው ትተነው በዛሬው ላይ እናተኩር።

የሀገራችን በኩረ ሥልጣኔ በሆነው ትግራይ ክፍለ-ሃገር ተወልደው ኢትዮጵያ እንድትበታተን ላለፉት 34 ዓመታት ወያኔዎች የፈፀሙት በደል በታሪክ መዝገባችን ዉስጥ '' አሳፋሪ '' በሚለው ምዕራፍ ውስጥ ተመዝግቦ ቀጣዩ ትውልድ እንዲመለከተው መሆኑ የትግራይ ክፍለ ሃገር ተወላጆችን ብቻም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሁሉ አንገት የሚያስደፋ ነው። ይህ ኣሳፋሪ ታሪክ እንዳይደገም ዛሬ ሁላችንም ያለፈውን ጥፋት ይቅር ስለ ኢትዮጵያ ተባብለን ተቆራርሳ የቀረችው አገራችን ጨርሳ ሳትጠፋ በውጭም ሆነ በውስጥ ያለነው ልጆቿ ባስቸኳይ ተባብረን ልናድናት ይገባል። ሰሞኑን ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በጽሑፍና በፓልቶክ ያቀረቡት ጥሪም ይህን ያገር አድን ጥሪ ነው። በአቶ መልስ ከሚመራው ወያኔ በስተቀር ለኢትዮጵያ ሌላ የውስጥ ጠላት እንደሌላት ተገንዝበን ይህን የጋራ ጠላት በሚታገሉት መካከል መሠረታዊ የሆነ ልዩነት እንደሌለ ሁላቸንም ተገንዝበን ክፍፍልና ከፋፋይ ሥዓትን  ድል ለመምታት የተባበረ ክንዳችን እናንሳ !

ኢትዮጵያ በልጆቿ ትብብር ከወደቀችበት ትነሳለች !

ከልጆቿ አንዱ ድሉ ዘገዬ ዘወእቱ ስምዓ ጽድቅ